# <u>በውስጥም በውጭም ሀገራችንን በተመለከተ ያለው ሁኔታ</u>

(ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ የቀረበ ሀተታ፣ መስከረም 2004)

አልታደልምና ትላንትም ዛሬም መጃጃልን የመረጡ ዜጎች መድረኩን ይዘው ከፀረ ወያኔ ተልዕኮአችን ሊያደናቅፉን እየጣሩ ናቸው። አረመኔውን ደርግ ጊዜ እንስጠው ያሉትን አንረሳም። ፀረ-ኢትዮጵያው ወያኔም ለሥልጣን ሲበቃ ለልጆቻችን ጊዜ ስጡ ብለው የተማፀኑትንም መቸም የምንረሳቸው አይሆንም ።

ለወያኔ ጊዜ መስጠት ሳይሆን ጊዜን መንሳት ነበር ግዴታችን። አልሆነምና ከ20 ዓመት በላይ ተወዘፈብን። በአፋኝነቱ ብቻ ሳይሆን በራሳችንም ድክመት። ተቃዋሚ የተባለው ተወናብዶና ወይም በባዕድ ተፅዕኖ ስር ወድቆ ሀቀኛ ተቃዋሚ ማድረግ ያለበትን ማድረግ ስለተሳነው። ተቃዋሚ የተባለው የባዕድን ትዕዛዝና መመሪያ መቀበል ተልዕኮው በመሆኑ። ተቃዋሚ የተባለው ጠላትና ወዳጅን መለየት አቅቶት ከጠላት ጋር በመተቃቀፉ። ማበር የሚችሉ ተቃዋሚዎች በዚህ በዚያ ምክንያቶች ሊያብሩ ባለመቻላቸው። ተቃዋሚ በሚልሽፋንም ኢምንት የሆኑና ሚዛን የማይደፉ ምትሐት ቡድኖች መድረኩን በመያዛቸው ። ተቃዋሚ ተብዬው ጎራ በአስመሳዮችና አባል አልባ በሆኑ መጨናነቁ ውስጣዊ ችግርን ማባባሱ ሀቅና የሚካድ አይደለም ። መጀመሪያ ከራስ ድክመት መነሳቱ ተገቢ ነውና የሕዝብ ትግል ዋናው ደንቃራው ተቃዋሚና ታጋይ የሚባሉት ክፍሎች ናቸው። ለምን?

- የተቃዋሚው ጎራ በደርግ ወንጀለኞች በመጨናነቁ ፤
- የተቃዋሚው ጎራ በአፍቅሮ ወያኔ በተያዙ አስመሳይ ታጋዮች በመያዙ፤
- ነገ ሕዝባዊ ፍርድ ይጠብቀናል ብለው የሚሰጉ በውስጥ ውስጥ ከወያኔ ማበሩን በመምረጣቸው፤
- ዋናው ግን  በሆነው ምክንያት የተነሳ የወያኔን መወገድ የማይፈልጉ ሆነው በመገኘታቸው ነው።

ባዕዳን የወያኔ አገዛዝ ማለትም ፖለቲካውና አቅዋሙ-- መለሰ ኖረ ሞተ-- እንዲቀጥል ይፈልጋሉ። ታማኝ ሎሌንና ቡችላን ማን ይጠላል? ስለዚህም ስርዓቱ ሳይናጋ መቀጠሉ - ለጥቅማቸው አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ልፍስፍስ የሆኑ ተቃዋሚ ነን ባዮችን በስርዓቱ ዙሪያ ለመኮልኮል ይጥራሉ። ለአዲሱ ሰውዬ ጊዜ እንስጠው፣ ለውጥ መጥቷል፣ ወዘተ ብለው እየለፈፉ ራሳቸውን እንዲያዋርዱ ያደርጓቸዋል። ራሳቸውን ሲያታልሉና ሲያቀሉ ሕዝብን ያደናገሩ እየመሰላቸው ወያኔ ሞርዶ ወደፊት ያመጣውን ስልጣንና ጡንቻ አልባ  አዲስ ጠቅላይ ሚኒስቴር ተብዬ ነፃ ባለስልጣን አስመስለው ለማቅረብ ደፋ ቀና ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ሳያፍሩ ለመለስ ሞት አለቀስን አዘንን፣ ደበንን ብለው ሙሾ ያ

ወርዱ ዘንድ ይገደዳሉ:: ሁሉም ተጠራቅሞ የማፈሪያዎችና የሀገር አዋራጆች ጫጫታ ነው:: ሁሉ
ም ተደማምሮ የከሀዲ ዋይ ዋይታ ነው ::

ዛሬ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ለውጥ መምጣቱን የሚያበስረው የወያኔን ቀውስና ንትርክ በመከሰቱ ነ
ው:: መለስን ተኪ ወያኔ ላይ መስማማት በማቃቱ ያለው ይቀጥል ተከፋፍለን ሌሎች ከሚበሉን በ
ሚል ነው የደሳለኝ ልጅ ይቀጥል የተባለው:: ሀይለማርያም ደሳለኝ ወሳኝ ለመሆን የሚችልበት ምን
ም ሁኔታ የለም:: ባለ ጡንቻ ድርጅት የለው ፣ ጦሩንአፋኝ መዋቅሮችን አይቆጣጠር፣ የኤኮኖሚ አ
ውታሮችን አልያዘ ወዘተ ... ሁሉም በወያኔ ቁጥጥር ስር ነው:: ሰለዚህም ሚናው ዕዝ ተቀባይነትና
ጉዳይ አስፈፃሚነት ነው:: ለፕሬዚዳንቱ የተሰጠውንሚና ወራሽ ነው እንጂ መለስን ተኪ አይደለም::
ለዚህም ነው ሀይለማርያም ያልሆነውን ሆነ፣ የሌለውን ስልጣን ያዘ ብለው ሊነግሩን የሚፈልጉት ሁ
ሉ ወደዱም ጠሉም የወያኔ ገደል ማሚቴዎች ሆነው የሚገኙት:: አደናጋሪዎች፣ አታላዮች ፣ እሽሩ
ሩረ ብለው አስተኚዎች :: የወያኔ ውስጣዊ ቀውስ ተካሮ መገኘቱ ምናልባትም ለመጪው ምርጫ ቧ
ልታቸው ሳይደርሱ የሚበጣበጠበትን ሁኔታ የሚጠቁም ይሆናል:: በድንገተኛ የጄኔራሎች ሹመት
ስብሐት ነጋ የበላይነትን ሲይዝ የነበረከት-አዜብ ጎን መጠቃቱን ያመለክታል:: አክራሪው አባይ ወል
ዱም የወያኔ ሊቀ መንበር  መባሉ ለበረከት ቡድንና ለጌቶቹ ቸር ወሬ አይደለም:: ሰብሐት ነጋና መ
ሰሎቹ ትግሬዎች በረከትና መሰሎቹን ማን ፈጥሯችሁ ባይ ናቸው:: ይህ የወያኔ የከረረና ሊዳፍን የ
ማይችል ቅራኔ ለሀገር ወዳዶች ሰፊ ቀዳዳን ይሰጣል:: በዚህ መጠቀም መቻል አለመቻላቸውም ወሳ
ኝ ይሆናል:: ለዚህም ነው የባዕድ ቅጥረኞች ሆነውና ከሀዲ ሆነው የሕዝብንየበላይነት ለማደናቀፍ ከ
ስርዓቱና ከባዕዳን ጋር የሚያብሩት ሁሉ ፀረ ኢትዮጵያ ሆነው የሚፈረጁት:: ለሀይለማርያም ጊዜ እ
ንስጠው ፣ ዕርቅን እንሻ ፣ መሰረታዊ ለውጥ ብለን አናክር ወዘተ እያሉ የሚጮሁት ሀገር ወዳድ ሳይ
ሆኑ ለባዕድና ለስርዓቱ ያደሩ ከርሳሞች ናቸው ::

በተጨባጩ ሁኔታ ዙሪያ ባዕዳን ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እየጣሩ ናቸው :: አሜሪካና ምዕራባውያን
አቅፍፈው ደግፈው ያቆዩት ቡችላ አገዛዛቸው በመለስ ሞት የተነሳ እንዳይለወጥ ይፈልጋሉ:: ኢትዮ
ጵያን መፈንጫቸውና መጫወቻቸው አድርገው መቀጥልን ይመኛሉናለውጥን አይወዱም:: ስለዚህም
በአገዛዙ ዘንድ ያሏቸውና ተቃዋሚ በሚል ሽፋን የሚያዟቸውን ሁሉ  በመመሪያ ማኳተን ይፈልጋሉ
:: ሀገር ወዳዶች ፀረ ወያኔ በሆነ ትግል ተጉዘውና ፀንተው መሰረታዊ የስርዓት ለውጥ እንዳያመጡጊ
ዜ እንስጥ ፣ እርቅወሰላም፣ አብዮታዊ ለውጥ አይጠቅምም ፣ መለስ ከሄደ ለውጥ ይቻላል ወዘተ በሚ
ል ሕዝብና ተቃዋሚውን አደናግረው ለገዢውና ቅጥረኛው ቡድን ጊዜ ሊለግሱትና ሊያጠናክሩት እ
የጣሩ ናቸው:: ይህን ሴራ ማወቅና ማክሸፍ ያስፈልጋል:: የሩቁ ብቻ ሳይሆን የአካባቢው በተለይ የ
ኢትዮጵያን ሕዝብ የመሰረታዊ ለውጥ ፍላጎት ሊያፍን እየተሯሯጠ ነው::  ከሰሜኑ ብንነሳ አያሌ የ
ሻዕቢያ ደጋፊዎች በመለስ ሞት ማዘናቸው የታየ ነው:: ወጣም ወረደም መለስ ለኤርትራ ህልውና
ጠበ ሆኖ መቆየቱ፣ የኢሳያስ ተቃዋሚዎች ብረት ይዘው እንዳይዘምቱ ማገዱ ወዘተ የታወቀ ነው::

ኢሳያስም ቢሆን የመለስ ተቃዋሚ ብሎ የሰበሰባቸውን አዳከመ በታተነ እንጂ አንዳቸውም ህልው ሆ
ነው የረባ ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴ ማድረግ አልቻሉም፡፡ ዕድሜ ለኢሳያስ ኦነግ ለአራት ተከፈለ፤ አርበ
ኞች ግንባር ተበታታነ፤ መሪዎቹ ተገደሉ ደብዛቸው ጠፋ፤ የትግራይ እንቅስቃሴ ያሉት በኤርትራ
መሬት በወያኔ ተገደሉ ፤ እርዳን ብለው የተማጠኑ ሌሎች የዋሆችም መና ቀሩ፡፡ ኢሳያስ ለመለስ መ
ለስ ለኢሳያሰ ቆመው ባጅተዋልና መለስ ሲሞት የእሱን ፖለቲካ የማይከተሉ የትግራይ ብሔረተኞች
ከመጡ ጉዴ ፈላ ባዩ ሻዕቢያ በስጋት ላይ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ሻዕቢያ 50 ዓመት ላለፉቸው
ሽማግሌዎች ሁሉ ጠመንጃ መሰጠት መጀመሩ ምን ያሳያል? ወደ አካባቢያችን ሁኔታ ስንመጣ በሩ
ቁ ያሉ ምዕራባውያን እያሴሩብን እንዳሉ ሁሉ የቅርቦቹም አልተኙልንም፡፡ የሱዳኑ በሺርና የግብፅ
አዲሰ መሪ ተገናኝተው በአባይ ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ አንደሚስማሙ ገልጠዋል፡፡ ሱዳን ኢትዮጵ
ያን ግብፅ ልትወር ትችል ዘንድ የጦር ሰፈር መስጠቷ ምስጢር አይደለም፡፡ ለዚችው ሱዳን ነው ከ
ሀዲው መለሰ የሀገራችንን መሬት አሳልፎ የሰጠው፡፡ ይኸው መለስ የአሜሪካንን ጥቅም ለማስጠበቅ
ሶማሊያን በመውረሩ ፤ ለአሜሪካ የጦር አይሮፕላን ቤዝ አምባ በአርባ ምንጭ በመስጠቱ ወዘተ የጎረ
ቤት ሀገሮችን ጠላትነት አባብሶብናል፤ ለአደጋም አጋልጦናል፡፡ ከኢትዮጵያ ብሔራዊጥቅም አንፃር
አቅዋም መያዝ ሲገባን ከብዙዎች እንድንጋጭና ለአደጋም እንድንጋለጥ ሆነናል፡፡ ማለትም ዛሬ የኢ
ትዮጵያ ጠላቶች በዝተዋል፡፡ እነዚህም ሁሉ ዛሬ ከመሰለ ሞት ሊያተርፉ እየጣሩ መሆናቸው መታ
ወቅ ያለበት ሀቅ ነው፡፡

ለዚህም ነው የሀገር ዜጎች ተጨባጩን ሁኔታ ከሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከአካባቢና ዓለም አቀፉ ሁ
ኔታ ጋር አገናዝበው መመልከት ግዴታቸወ የሚሆነው፡፡ ዛሬ ዕርቅ ሰባኪዎች እነማን እንደሆኑ መገ
ንዘብ እንደሚገባን ሁሉ በዚህም በዚያም ሊጠቀሙብን የሚጥሩትንም ማወቅ ግዴታችን ይሆናል፡፡
መነሻችንና ዓላማችን የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትንና የሕዝቧ የዴሞክራሲ ፍላጎት መሟላት መሆን አለበ
ት፡፡ በዚህ ላይ ወለም ዘለም ከመጣ ሀገርና ሕዝብ ይጎዳሉ ፡፡ዛሬ ለእኛ የተሰወረ አይደለም -- የባዕድ
ቅጥረኞች ከተኙበት ተነስተው ሕዝባዊ አመፅን ለማፈን እየተራወጡ ናቸው፡፡ እናውቃቸዋልና ሊያ
ደናገሩን አይገባም፡፡ ተዉ ለወያኔ ስርዓት መውደም አትታገሉ እያሉን ናቸው፡፡ በተቃዋሚ ጭምብ
ልም ይህንኑ የሚለፍፉ አሉ፡፡ ጊዜ ማለፉን አልተረዱም፡፡ ከአንግዲህ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ ከውድቀ
ት የሚያድነው ማንም የለም፡፡ የተሰበረ የሸክላ ድስት ነው -- ፍርክስክቱ ወጥቷል፡፡ ተሰብስበን ወደ
ትቢያ መጣሉ የእኛ ፈንታ ነው፡፡ የሀገር ውስጠም የባዕዳንንም ሴራ ማክሸፉ የእኛ ስራና ግዴታ ነ
ው -- ኢትዮጵያ ሀራችን ናትና፡፡ እንወዳታለንና፡፡ ሌላ ሀገር የለንምና፡፡ ባንዳና ቅጥረኛ አይደለንም
ና፡፡ አሜሪካኖች ወይም ባዕድ ሳንሆን የማንቀየር የማንበገር ፅኑ ኢትዮጵያዊያን ነንና!

ፀረ ኢትዮጵያ ቅጥረኞችንና ሀገር አጥፊ ባዕዳንን እንታገላቸው !
ኢትዮጵያ የሀገር ወዳድ ጀግኖች ሀገር መሆኗን በገቢር እናስተምራቸው !
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!!